የኮ/መ/ቁ 286093

ቀን 24/08/2014 ዓ.ም

# የልደታ ምድብ 11ኛ ወንጀል ችሎት

## ዳኛ፡- አይናለም ደረጀ

ከሳሽ፡- የፌ/ጠ/ዐ/ሕግ - ቤተልሄም ጌታሁን ቀረቡ

ተከሳሾች- 1.ታረቀኝ ሙሉ ካጨሮ - ቀረቡ

2. ደስታ መስፍን መኮንን- ቀረቡ

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ሲሆን ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ከሳሽ ዓ/ሕግ ነሐሴ 25 ቀን 2012 ዓ.ም ፅፎ ባቀረበው ክስ ተከሳሾሽ የወ/ህ/አ 32(1)(ሀ) እና በሰው የመነገድ እና ሰውን በህግ ወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣውን አዋጅ ቁጥር 1178/2012 አንቀፅ 14(1) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ተከሳሾች በሰው የመነገድ እና ሰውን በህገወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀል በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 284774 በተከሰሰበት እና ኪዳኔ ዘካሪያስ መዝገብ የሰው ማስረጃ ሆነው በማስረጃ ዝርዝር ለቀረቡ የዓ/ሕግ ምስክሮች ለእያንዳንዳቸው 500000 ብር (አምስት መቶ ሺ.ህ ብር) እንደሚከፈላቸው ፍ/ቤት ቀረበችሁ በፖሊስ ጣቢያ የሰጣችሁትን ቃል ብትክዱ የሚደርሳባቸው ነገር የሌለ ስለመሆኑ የፌ/ከ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 153228 የሰጠው አስገዳጅ ውሳኔ እንደመለከቱ እና በክርክር ሂደት በፍ/ቤት ምስክር ሆነው እንዳይቀርቡ ወይም በችሎት ቀርበው የምስክርነት ቃላቸውን እንዲቀሩ ለማድረግ በማሰብ 1ኛ ተከሳሽ በ/ሕግ የማስረጃ ዝርዝር ስር በተራ ቁጥር 2ኛ ላይ የተጠቀሱትን ምስክር በነሐሴ 3

ቀን 2012 ዓ.ም ከቀኑ 9:30 ሰዓት ሲሆን ከምሽቱ በኪዳኔ ዘካርያስ ጉዳይ እንደወያያለን በሚል ከዚህ በላይ በተጠቀሰው የተከሳሽ ኪዳኔ ካርያስ መዝገብ ምስክር የሆኑትን በዓ/ሕግ የማስረጃ ዝርዝር ላይ በተራ ቁጥር 1ኛ. 4ኛ 6ኛ ላይ የተጠቀሱትን በአንድ ላይ አካል በማገኘት እናንተ ኪዳኔ ላይ መስክራችሁ የምትመጡት ለውጥ የለም አናንተን የሚጠቅማቸው ገንዘቡ ነው እንዳንዳንዳችሁ ያወጣችሁትን 500,000 ብር ኪዳኔ በእኔ አማካኝነት ይከፈላችኂል ፍ/ቤት ቀርባችሁ ሊባያ ላይ ሳያስቃየን የነበረው ሌላ ሰው ነው ኪዳኔን እናውቃውም ብላችሁ ካዱ ፍ/ቤት ምስክር ለመስማት የሰጠው ቀጠሮ እየደረሰ ስለሆነ ቀኑ ከመድረሱ በፊት መጨረሻ አለብን በማለት ካግባባቸው በኂላ በነሐሴ 4 ቀን 2012 ዓ.ም ከምሽቱ 1:00 ሰዓት በቂርቆስ ክ/ከተማ በሚገኘው አብሔም የተባለ ካፌ ውስጥ በዓ/ሕግ የማስረጃ ዝርዝር ላይ በተራ ቁጥር 1ኛ፣ 2ኛ፣ 3ኛ 4ኛ፣5ኛ የተጠቀሱትን በአካል በማግኘት ለእናንተ የሚሻላችሁ ገንዘቡን ወስዳችሁ ብትጠቀሙበት ነው በኤግዝቢትነት የተያዘ የኪዳኔ ገንዘብም ሆነ ንብረት የለም ካሳ ይከፈላችሁ ቢባል እንኳን ሊከፈላችሁ አይችልም በማለት ከነገራችው በኂላ በቀን ነሐሴ 6 ቀን 2012 ዓ.ም 1ኛ፣ 2ኛ፣ 4ኛ እና 6ኛ ተራ ቁጥር ላይ ለተጠቀሱት የዓ/ሕግ ምስክሮች ሄኖክ ከተባለ የአባቱ ስም የማይታወቅ ኪዳኔ ዘካርያስ ወንድም ከዱባይ ለእናንተ የማከፈል 1,200.000 ብር በእኔ እና በእህቴ እታለም ሙሉ ስም የተከፈተ መሆኑን ከነገራቸው በኂላ በነሐሴ 07 ቀን 2012 ዓ.ም እናንተ እንድታምኑኝ 400,000 ብር በእጄ ይገፔ ስራ በማለት ነሐሴ 8 ቀን 2012 ዓ.ም የኪዳኔ ወንድም የሆነው ሄኖክ የአባቱ ስም የማይታወቅ 500,000 ብር እንዲከፈላቸው በስልክ በማደራደር በነሐሴ 10 ቀን 2012 ዓ.ም በዓ/ሕግ የማስረጃ ዝርዝር በተራ ቁጥር 1ኛ ላይ የተጠቀሱት ምስክር ስልክ በመደወል ፍ/ቤት ቀርባችሁ ከመከዳችሁ በፊት ለእያንዳንዳችሁ 20,000 ብር ከካዳችሁ በኂላ ደግሞ 300,000 ብር እንከፈላችኂላን በፍ/ቤት ቀርባችሁ ብትከዱ የሚደርስባችሁ ነገር የሌለ ስለመሆኑ የኪዳኔ ጠበቃ ያስረዳችኂል በማለት እና ከ2ኛ ተከሳሽ ጋር እንዳገኛኙ ያደረገ ሲሆን ለምስክሮቹ የሚከፈለው ገንዘብ በራሱ ስም በተከፈተው በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሂሳብ ቁጥር 1000088028248 ነሐሴ 5 ቀን 2012 ዓ.ም 600000 ብር እንዲሁም እታለም ሙሉ ካሜሮ በተባለች እህቱ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

በሂሳብ ቁጥር 1000229420098 ነሐሴ 5 ቀን 2012 ዓ.ም 600,000 ብር ከኪዳኔ ገ/እግዚአብሔር በተባለች ግለሰብ ገቢ የተደረገላቸው በመሆን 2ኛ ተከሰሽም በቂርቆስ ክ/ከተማ ሚክሲኮ ደብረ ወርቅ ህንፃ አከባቢ በነሐሴ 6 ቀን 2012 ዓ.ም በግምት ከምሽቱ 12:00 ሰዓት ሲሆን ከዚህ በላይ በተጠቀሰው መዝገብ የተከሳሽ ኪዳኔ ዘካሪያስ ጠበቃ ሆኖ እያለ በዚሁ መዝገብ ምስክሮችን የሆኑትን ዓ/ሕግ የማስረጃ ዝርዝር ላይ በተራ ቀጥር 1ኛ እና 2ኛ ላይ የተጠቀሱትን ምስክሮች ከ1ኛ ተከሳሽ ጋር በአንድ ላይ በአካል በማግኘት የፍ/ቤት ቀጠሮ ቀን ፍ/ቤት ቀርባችሁ በፖሊስ ጣቢያ የሰጠችሁትን ቃል ብትቀይሩ ማለትም ኪዳኔ ዘካሪያስን እናውቀውም ተመሳስሎብን እንጂ አይተነው አናዋቅም ሲቢያ ላይ እያለን እናወቀውም ህገወጥ የሰዎች አዘዋዋር ተያዘ ሲባል ስሞትን ቃል ሰጠን እንጂ የምናውቀው ነገር የለም በማለት የምስክርነት ቃላቸውን ብትሰጡ በእናንተ ላይ ፍ/ቤት የሚያመጣው ነገር የለም ኪዳኔ ነፃ ይወጣል እናንተም ገንዘባችሁን ታገኛላችሁ ቀጠሮውን 2ኛው የኪዳኔ ጠበቃ ከኮረና ተጠርጥሮ አልቀረበም በሚል ፍ/ቤቱ ምስክር ለመስማት የሰጠውን ቀጠሮ ያስለወጥኩት ከእናንተ ጋር ለመደራደር እንዲያመችን ነው በማለት በአጠቃላይ ተከሳሾች ምስክሮች በፍ/ቤት የክርክር ሂደት ምስክር ሆነው እንዳይቀርቡ በማይገባ በጥቅም በደለል ጣልቃ በመግባት የከላከሉ በመሆኑ በፈፀሙት በዋና ወንጀል አድራጊነት ተከፋይ በመሆን በጠቃሚዎች እና ምስክሮች ላይ የሚፈፀም ወንጀል ተከሰዋል በማለት በማስረጃነት የሰው እና የሰነድ ማስረጃችን አቀርቧል ተከሳሾች የቀረበበቸውን ክስ እና ማስረጃ እንዲደርሳቸው ተደርጎ በችሎት ከተነበበላቸው እና እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ የክስ መቃወሚያ ካላቸው ተጠይቁ እያንዳንዳቸው ተከሳሾች የክስ መቃወሚያቸውን አቅርበው ፍ/ቤት በ17/02/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተከሳሾች ያቀረቧቸውን የክስ መቃወሚያዎች ባለመቀበል ብይን ሰጥቷል፡፡ በመቀጠልም ተከሳሾች የእምነት ክህደት ቃላቸውን እንዲሰጡ ሲጠየቁ ሁለቱም ተከሳሾች የወንጀል ድርጊቱን አልፈፀምንም ጥፋተኛ አይደለም በማለት ክደው የተከራከሩ በመሆን ፍ/ቤቱ የዓ/ሕግን ምስክሮች አድምጦ በዓ/ሕግ በኩል የቀረቡ ማስረጃዎችን መርምሮ ተከሳሾች የቀረበባቸውን ክስ እና ማሰረጃ እንዲከላከሉ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 142(1) መሰረት ብይን ሰጥቷል በተሰጠው ብይን

መሰረት ተከሳሾች የመ/ምስከሮችን እና የሰነድ ማስረጃ አቅርበው የመ/ምስክሮቻቸውን ተሰምተዋል፡፡

ፍ/ቤቱም እያንዳንዱ ተከሳሾች በስማቸው መ/ምስክሮች በዓ/ሕግ በኩል የቀረበባቸውን ክስ እና ማስረጃ ተከለከለዋል? ወይስ አልተከላከሉም? የሚለውን ጭብጥ በሚያዝ መዝገቡን ከቀረቡት ማሰረጃዎች እና አግባብነት ካለው የህጉ ድንጋጌ ጋር በማናዘብ መርምሯል ዓ/ሕግ በተከሳሾች ላይ የወ/ህ/አ 32(1)(ሀ) እና በአዋጅ ቁጥር 1178/2012 አንቀፅ 14(1) ስር የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ ምስክሮች በፍ/ቤት የክርክር ሂደት ምስክር ሆነው እንዳይቀረቡ በማይገባ ጥቅም በመደለል ጣልቃ በመገባት የከላከሉ በመሆን በዋና ወንጀል አድራጊነት ተከፋይ በመሆን በጠቋሚዎች እና በምስክሮች ላይ የሚፈፀም ወንጀል ፈፅመዋል በማለት ሲሆን እያንዳንዱ ተከሳሾች የወንጀል ድርጊቱን አልፈፀምንም በማለት ክደው በመከራከራቸው ዓ/ሕግ ምስከሮቻቸው አቅርቦ አሰምቶ ፍ/ቤቱም የቀረቡትን ምስክሮች ቃል እና የቀረበውን የሰነድ ማስረጃዎች ከመረመረ በኋላ ተከሳሾች የቀረበባቸውን ክስ እና ማስረጃ እንዲከላከሉ በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 142(1) መሰረት ነሐሴ 4 ቀን 2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት ብይን ሰጥቷል፡፡

በዚህ ብይን መሰረት እያንዳንዱ ተከሳሾች ያቀረቧቸውን የወንጀል ድርጊት ያልፈፀሙ መሆኑን ይከላከልልናል ያሏቸን መ/ምስክሮች በየበኩላቸው መ/ምስክሮች ያስረዳሉ የሚሉትን ጭብጥ በማሰያዝ መ/ምስክሮቻቸውን አቀርበው አሰምተዋል፡፡

ተከሳሾች መ/ምስክሮች ያሰረዱልናል በማለት ያስያዙት ጭብጥእ ሆነ ያሰሟችው መ/ምስክሮች የተለያዩ በመሆናቸውን እደንዳንዱ ተከሳሾች በዓ/ሕግ በኩል የቀረቡትን ክስ እና ማስረጃ ተከላክለዋል ወይስ አልተከላከሉም? በሚለው ጭብጥ ላይ ውሳኔ ለመስጠት እያንዳንዱ ተከሳሾች ያስያዙትን ጭብጭ እና የስሟቸውን መ/ምስከሮች ለየብቻ መመርመር ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

አንድ የወንጀል ድርጊት ፈፅሟል ተብሎ ክስ የቀረበበትን ተከሳሾ ዓ/ሕግ ተከሳሹ የተከሰሰበትን የወጀንል ድርጊት መፈፀሙን በበቂ ሁኔታ ማስረዳቱ ተረጋግጦ ተከሳሾች

የቀረበባትን ክስ እና ማስረጃ እንዳከላከል ብይን ከተሰጠ በኋላ ተከሳሽ የመ/ማስረጃ በማቅረብ በዓ/ሕግ በኩል የቀረበበትን ክስ እና ማስረጃ ተከላክሏል የወንጀል ድርጊቱን አለመፈፀሙን አስይቷል የሚለውን ተከሳሹ የተከሰሰበትን እና ተከላከል የተባለበትን የወንጀል ድርጊት ተፈፅሟል ተብሎ በክሱ ላይ በተገለፀው ጊዜ ቦታ እና የወንጀል ድርጊት አፈፃፀም ሁኔታ ወንጀሉን ያልፈፀመ መሆኑን ወንጀሉን ተፈፀመ በተባለበት ጊዜ እና ቦታም ያልተገኘ ወይም ከቦታው ላይ ቢገኝም የተገለፀውን ወንጀል ያልፈፀመ መሆኑን በሚያሳይ መልኩ ማስረዳት ከቻለ ወይም በዓ/ሕግ ማስረጃ ላይ ምክንያታዊ ሊባል የሚችል እና የወንጀል ድርጊቱን ለመፈፀሙን ሊያሳይ በሚችል ሁኔታ ጥርጣሬ መፍጠር የቻለ ከሆነ ይህም ተገቢነት ታዓማኒነት ወይም እምነት ለጣልበት የሚችል አይነት ማስረጃ አቅርባ መሰማት የቻለ ከሆነ ነው፡፡

ከዚህ አኳያ በተከሳሾች በኩል የተሰሙ መ/ምስክሮች ቃል እና በ2ኛ ተከሳሽ የቀረቡትን የሰነድ ማስረጃዎች ስንመለከተ በቅድሚያ የ1ኛ ተከሳሽን መ/ማስረጃ ስንመለከት 1ኛ ተከሳሽን አንድ መ/ምስክር ያሰሙ ሲሆን መ/ምስከሩ ያስረዳሉ በማለት ጭብጥ ያስያዙትም 1ኛ ተከሳሽ ምስክሮችን ለመደለል ገንዘብ ያላደረደሩ መሆኑን በአቶ ኪዳኔ ዘካርያስ መዝገብ የዓ/ሕግ ምስክሮች የሆኑት አቶ አቤል እና አቶ ዳንኤል የተሉት እያንዳንዳን ቤተሰቦቻችን ብር 500,000 በላይ ያወጡ ስለሆነ ይህን ገንዘብ ይከፈለን በማለት በራሳቸው አነሳሽነት 1ኛ ተከሳሽን ጠይቀው 1ኛ ተከሳሽም ዱባይ ለሚኖረው ለአቶ ኪዳኔ ዘካርያስ ወንድም በኢሞ ስልክ ደውሎ የዓ/ሕግ ምስክሮች ያገኙት መሆኑን ከዚህ ወጪ የፈፀሙት ድርጊት የሚደርደር ተግባር የሌለ መሆኑን በተደጋጋሚ ጊዜ የዓ/ሕግ ምስክሮች የሆኑት እየመጡ 1ኛ ተከሳሽን ሲጠይቁተ 1ኛ ተከሳሽም በኢሞ ብቻ ለአቶ ኪዳኔ ዘካርያስ ወንድም በመደወል አናንተ አውሩ በማለት በስልክ ብቻ ያገናኟቸው መሆኑን ይህ ገንዘብም ለምስክር ማበያያነት ሳይሆን ቤተሰብ ላወጣው ወጪ መሆኑን ያስረዳሉ በማለት በፍ/ቤት ጠያቂነት ጭምር ዝርዝር የሆነ ጭበጥ አስመዝግበዋል መ/ምስክሩም ቀርበው 1ኛ ተከሳሽ አብሮ አደነ ጓደኞቸው መሆናቸውን ከስራ ሰዓት ወጪ ብዙ ጊዜ የሚገናኙ መሆኑን በነሐሴ ወር 2012 ዓ.ም መጨረሻ አከባቢ አቤል እና ዳንኤል የሚባሉ

ልጃችን በተደጋጋሚ ከ1ኛ ተከሳሽ ጋር የሚያገኗቸው መሆኑን ሲመጡም የሚያገኛቸው አቤም በሚባል ካፌ ላይ መሆኑን መጥተው ከ1ኛ ተከሳሽ ጋር የሚያወረት እና የሚደረደሩት ስለ ብር ጉዳይ መሆኑን የሚሉትም ቤተሰባችን ያወጣው ብር 500,000 አለ ይህን ብር ይሰጠን ሲሉ የሚሰሙ መሆኑን 1ኛ ተከሳሽ ምንም የሚናገረው ነገር የሌለ መሆኑን በኢሞ እየደወለ በስልክ ብቻ የሚያገቻው መሆኑን ሁለቱም ልጃቸው መጥተው 1ኛ ተከሳሽን እንዴት እንደረክልን በማለት የሚጠይቁት መሆኑን 1ኛ ተከሳሽ ኪዳኔ ወንድም ጋር ስልክ እየደወለ የሚያገናኘቸው መሆኑን በኋላም ጊዜው እየሄደ ስመጣ ደሞ ብር 700,000 ይከፈለን በማለት የጠየቁ መሆኑን ሰዎቹ በኋላ ላይ 1ኛ ተከሳሽን በስልክ ሪከርድ አድርገናል ለህግ እንሰጣለን በማለት ሲያስፈራሩት ከአሁን በኋላ ይህን ነገር አቁሚያለሁ እጄን አንስቻለሁ በማለት ምላሽ የሰጣቸው መሆኑን ምስክረዋል፡፡ መ/ምስክሩ የሰጡት ሙሉ የምስክርነት ቃልም ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

1ኛ ተከሳሽ የተከሰሰቡትን እና ፈፅመዋል ተብሎ በዓ/ሕግ ምስክሮች የተረጋገጠባቸውን የወንጀል ድርጊት ይህን ይከላከልኛል በማለት ያስያዙትን ጭብጥ መ/ምስክሩም የሰጡት ቃል በአድ ላይ የሚገናዘብ ስንመረመርም ደግሞ 1ኛ ተከሳሽ በክሱ ላይ በተገለፀው ሁኔታ በሰው መነገድ እና ሰውን በህግ ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀል በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 284774 በተከሰሱበት በእነ ኪዳኔ ዘከርያስ ላይ የዓ/ሕግ ምስክር የሆኑትን እና በዚህ መዝገብም የዓ/ሕግ ምስክር የሆኑትን 1ኛ እና 2ኛ ምስክሮች ስለገንዘብ ድርድር ሲያድርጉ የነበሩ መሆናቸውን መ/ምስከሩ አስረድተዋል፡፡መ/ምስክሩ 1ኛ ተከሳሽ እነዚህን ዓ/ሕግ ምስክሮች የሆኑ ያለበት መጥተው ስጠይቁት ስልክ በመደወል ብቻ ነው ሲያገናቸው የነበረው ሌላ የተናገረው ነገር የለም በማለት የገለፁ ተከሳሽም ይህን በጭብጥነት ያስያዙ ቢሆንም 1ኛ ተከሳሽከ ሌላ ሰው በተለይ ሁኔታ ምስክሮቹን በሚገኝት ዱባይ ላለው የኪዳኔ ዘካርያስ ወንድም ስልክ በመደወል እንዴት ማገናኘት ቻሉ አቶ ዳንኤል የተባሉት ምስክር የ1ኛ ተከሳሽ ዘመድ መሆናቸውን 1ኛ ተከሳሽ ምስክሮቹ ከገንዘዘብ ጋር በተያያዘ ድርድር እንዲያደርጉ በተደጋጋሚ ለምን ስልክ ደውሉ ስልከ መደወል ብቻ ከሆነ ለምን ራሳቸው የዓ/ሕግ ምስክሮች በራሳቸው

ስልክ ደውለው ማውራት አልቻሉም ለምን የ1ኛ ተከሳሽ መሀል ገብነት አስፈላጊ የሚሉትን ጉዳዮች ስንመለከት የኛ ተከሳሽ መ/ምስክር በእነዚህ መሰረታዊ በሆነ ጉዳዩ ላይ የሰጡ ምላሽ የለም ይህ ደግሞ የዓ/ሕግ ክስ እና ማስረጃ በይብልጥ  የሚያጠናክር 1ኛ ተከሳሽ በክሱ ላይ በተገለፀው የወንጀል ድርጊት አፈፃፀም ሁኔታ ገንዘብ የዓ/ሕግ ምስክሮች ተቀብለው የምስክርነት ቃላቸውን በፍ/ቤት ቀርበው እንዳይሰጡ የምከለከል ተግባር ሲፈፅሙ የነበረ መሆኑን አረጋገጫ ነው፡፡

መ/ምስክሩ 1ኛ ተከሳሽ እጄን ከዚህ ጉዳይ አንስቻለሁ ያሉት ምስክሮቹ 1ኛ ተከሳሽ በስልክ ቀድተው ማስፈራራት ሲጀምሩ እና ጊዜውም እየሄደ ስመጣ እንደሆነ ገልፀዋል  ይህ ደግም በዓ/ህግ  ምስክሮች ጭምር 2ኛ ተከሳሽ ምስክሮች በፍ/ቤት ቀረበው እንዳይመሰክሩ ሲናገሩ በስልክ የተቀዱ መሆኑን ተመስክሯል በአጠቃላይ 1ኛ ተከሳሽ በሰማቸው መ/ምስክር የተከሰሱበትን የወንጀል ድርጊት ያልፈፀሙ መሆኑን ወይም አለመፈፀማቸውን ሊያሳይ በሚችል እና በዓ/ሕግ ማስረጃ ላይ ጥርጣሬ በሚፈጥር መልኩ ያላስረዱ ይልቁንም በዓ/ሕግ በኩል የቀረበውን ማስረጃ  የሚደግፍ እና በሚያጠናክር መልኩ ያስረዱ በመሆኑ ፍ/ቤቱ የ1ኛ ተከሳሽ በዓ/ሕግ በኩል የቀረበባቸውን ክስ እነ ማስረጃ አልተከለከሉም በማለት በተከሰሱበት አዋጅ ቁጥር 1178/2012 አንቀፅ 14(1) የተመለከተውን ድንጋጌ በተመላለፍ ምስክሮች በፍ/ቤት የክርክር ሂደት ምስክር ሆነው እንዳይቀረቡ በማይገባ ጥቅም በመደለል ጣልቃ በመግባት በመከላከል ወንጀል ጥፋተኛ ናቸው በማለት በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 149 (1) መሰረት የጥፋተኝነት ፍርድ ሰጥቷል፡፡

በመቀጠልም የ2ኛ ተከሳሽ ያስያዙትን ጭብጥ እና መ/ምስክሮች ቃል ስንመለከት 2ኛ ተከሳሽ ጭብጥ ያስያዙትም ሆነ መ/ምስክሮቻቸውን ያሰሙት የሰነድ ማስረጃ ያቀረቡት በሁለት መልኩ ነው አንደኛው ዓ/ሕግ የወንጀል ድርጊት ፈፅመዋል ባለበት ጊዜ እና ቦታ ማለትም ነሐሴ 6 ቀን 2012 ዓ.ም ከምሽቱ 12፡00 ሰዓት ሚክሶኮ ደብረ ወርቅ ህንፃ አከባቢ ከቦታው ላይ አልነበርኩም የተባለውን ድርጊት አልፈፀምኩም የሚል ሲሆን ሌላው ጭብጥ ደግሞ በክሱ ላይ 2ኛ ተከሳሽ ፈፅሟል ተብሎ የተገለፀው ድርጊት እና 2ኛ ተከሳሽ ተላለፍዋል ተብሎ

የተጠቀሰው ድንጋጌ የወንጀል ድርጊት አያሟላም የተፈፀመ የወንጀል ድርጊት የለም የሚል ነው በሁለቱም ጭበጦች ተከሳሽ ራሳቸው ከሰጡት የተከሳሽነት ቃል በተጨማሪ መ/ምስክሮች አቅርበው አሰምተዋል፡፡ 2ኛ ተከሳሽ በመጀመሪያ ያስያዙትን በጭብጥ ማለትም የወንጀል ድርጊቱ ተፈፅሟል በተባበለት ጊዜ እና ቦታ አልተገኘሁም የወንጀል ድርጊቱንም አልተፈፀምኩም በማለት ያስያዙት ጭብጥ በተመለከተ ሁለት መ/ምስክሮችን ማለትም በመ/ማስረጃ ዝርዝር ላይ በተራ ቁጥር 5 እና 6 ላይ የተጠቀሱትን መ/ምስክሮች አቅርበው ያሰሙ ሲሆን እነዚህ መ/ምስክሮች ያስረዳሉ በማለት 2ኛ ተከሳሽ ያሰያዙት ጭበጥ ነሐሴ 6 ቀን 2012 ዓ.ም ከቀኑ 9፡00 አከባቢ ከ6ኛ መ/ምስክር ጋር ከኮበ ፅባህ ት/ቤት አከባቢ ተገናኝተው ወደ 2ኛ ተከሳሽ እህት መብራት መስፍን ታመው ስለነበረ ወደ ህክምና ለመውሰድ ወደ ቤት የሄዱ መሆኑን ከዚያም ከ2ኛ ተከሳሽ እህት ቤት እስከ 10፡30 አከባቢ ድረስ ቆይተው የ5ኛ መ/ምስክር ለፍቅረኛ ጋር የተገናኙበትን የአምስት አመት ጊዜ ለማክበር ወደ መገናኛ መሳብ ሀበሻ ወደ ሚባለው ሪስትራንት ሄደው ከዚያም እስከ ምሽቱ 1፡30 ድረስ ያመሹ መሆኑን በኋላም 6ኛ ምስክር በመኪናቸውን ወደ ወሰን ወደ ሚገኘው ቤታቸው ያደረሳቸው መሆኑን ያስረዳሉ በማለት ነው፡፡

5ኛ መ/ምስክር በዚህ ጭብጥ እና በሁለተኛው ጭብጥ ላይም የምስክርነት ቃላቸውን የሰጡ ሲሆን ይህን ጭብጥ በተመለከተ የሰጡትን ቃል ስንመለከት ነሐሴ 6 ቀን 2012 ዓ.ም ከፍቅረኛቸው ጋር የተገናኙበትን የአምስት አመት በግል ለማክበር መገናኛ ከሚገኘው መሰብ ሀበሻ ሬስቶራንስ ከሚባለው ሆቴል 2ኛ ተከሳሽ ከጓደኛቸው አቶ ብርሃነ ጋር ወደ 11፡00 አከባቢ መጥተው በዚያው ሲጫወቱ አምሽተው ከምሽቱ 1፡30 አከባቢ የሄዱ መሆኑን 2ኛ ተከሳሽ የስራ ጓደኛቸው የነበሩ በመሆኑ ልደታቸውን ሲከበርም ከቦታው የነበሩ መሆኑን የወንጀል ድርጊቱ ተፈፀመ በተባለበት ቦታ ሚክሲኮ ሲሆን 2 ተከሳሽ በጊዜው ከነበሩበት ቦታ አንፃር ወደ ሚክሲኮ ሊሄዱ የማችሉበት ሁኔታ ያልነበረ መሆኑን ከዚያው መገናኛ ያመሹ መሆኑን የመሰከሩ ሲሆን 6ኛው ም/ምስክር አቶ ብርሃነ ሀጉስ በሰጡት የመ/ምስክርነት ቃልም 2ኛ ተከሳሽ ጓደኛቸው መሆኑን ነሐሴ 6 ቀን 2012 ዓ.ም ቁሳቁም ስለነበረ ቤተክርስቲያን

ድረሰው የተመለሱ መሆኑን በኋላ ወደ 8፡20 አከባቢ 2ኛ ተከሳሽ ስልክ ደውሎ እህቴ ታማለች ህክምና እንውሰዳት ስል ጠይቃቸው መኪና ይዘው ስለነበር ከእህታቸው ጋር አብረው 2ኛ ተከሳሽ ወደነበረበት ኮከበፅባህ ት/ቤት አከባቢ የሄዱ መሆኑን ከዚያም ወደ 2ኛ ተከሳሽ እህት ቤት ሲገቡ የ2ኛ ተከሳሽ እህት ያመማቸው የእርግዝና ህመም በመሆኑ ከቤት ቡና ተፈልቶ እስከ 10፡30 አከባቢ የቆዩ መሆኑን ቡናውን ያፈላችው የ2ኛ ተከሳሽ እህት ሰራተኛ መሆኗን ከዚያም በወቅቱ ዝናብ ስለነበረ 2ኛ ተከሳሽ የጓደኛቸው ፕሮግራም ስላለ ወደ መገናኛ አድርሰን ብሎኝ እኔም በመኪና ይገፔው ሄጃለሁ 2ኛ ተከሳሽ በወቅቱ መኪና መንዳት አይችልም ከጓደኛቸው ጋር መገናኛ መስቦ ሀበሻ ሆቴል ከቀኑ 11፡00 አከባቢ ከተገናኙ በኋላ ልመለስ ሲል ጓደኛውን አቶ ሳሙኤል ተዋውቀው ብሎኝ ከተዋወቅን በኋላ አቶ ሳሙኤል አብረህ ትንሽ ቆይን ብሎ እኔም አብራያቸው ስጫወት እስከ 1፡30 ድረስ ቆይተናል ከዚህ በኋላም 2ኛ ተከሳሽ ወደ ወሰን አድርሰኝ ብሎኝ ወደ ቤቱ ወደ 2፡00 አከባቢ አድርሸዋለሁ በማለት የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡ ሁለቱም መ/ምስክሮች የሰጡት ሙሉ የመ/ምስክርነት ቃል ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

ከእነዚህም የመ/ምስክሮች ቃል 2ኛ ተከሳሽ ካስያዙት ጭበጥ እና በዓ/ሕግ በኩል የቀረበው ክስ እና ማስረጃ አኳያ ስንመለከት ደግሞ ዓ/ሕግ 2ኛ ተከሳሽ በክሱ ላይ የተገለፀውን የወንጀል ድርጊት ፈፅመዋል በማለት ክስ የቀረበው እና ምስክሮችም ያስረዱት ነሐሴ 6 ቀን 2012 ዓ.ም ከምሽቱ 12፡00 አከባቢ ሚክስኮ ደብረ ወርቅ ህንን አከባቢ ሲሆን በ2ኛ ተከሳሽ በኩል የተሰሙት መ/ምስክሮች ደግሞ ተመሳሳይነት ባለው የምስክርነት ቃል 2ኛ ተከሳሽ በዚህ የወንጀል ድርጊቱን ፈፅመዋል በተባለበት ቀን ማለትም ነሐሴ 6 ቀን 2012 ዓ.ም ከቀኑ 9፡00 እስከ ምሽቱ 2፡00 ድረስ ከ9፡00 -11፡00 በመጀመሪያ ቀበና አከባቢ ከዚያም ከ11፡00 እስከ ምሽቱ 1፡30 መገናኛ ከ1፡30 እስከምሽቱ 2፡00 ድረስ ወደ ወሰን አከባቢ ከመ/ምስክሮች ጋር የነበሩ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ይህ የመ/ምስክሮች ቃል ደግሞ 2ኛ ተከሳሽ በክሱ ላይ የተገለፀውን የወንጀል ድርጊት ያልፈፀሙ መሆናቸውን የሚያሳይ እና በዐ/ሕግ ክስ እና ማስረጃ ላይ ምክንያታዊ ጥርጣሬ የሚፈጥር መሆኑን ፍ/ቤቱ ተረድታል ይህ ደግሞ 2ኛ ተከሳሽ በክሱ

ላይ በተገለፀዉ ጊዜ እና ቦታ ተገኝተው  የወንጀል ድርጊቱን ያልፈፀሙ መሆናቸውን የሚያሳይ እና የሚያስረዳ የዓ/ህግ ክስ እና ማስረጃ የሚከለክል በመሆኑ ፍ/ቤቱ 2ኛ  ተከሳሽ በስማቸው እነዚህ መ/ምስክሮች በዓ/ሕግ በኩል የቀረበባቸውን ክስና ማስረጃ ተከለከለዋል በማለት በወ/መ/ሥሥ/ሕ/ቁ 149(2) መሰረት በነፃ እንዲሰናበቱ  ፍርድ   ሰጥቷል፡፡

2ኛ ተከሳሽ በአማራጭ በሁለተኝነት ያስያዙትን ጭበጥ በተመለከተ ማለትም ድርጊቱ ወንጀልን የሚያቋቁም አይደለምያሉትን በተመለከተ አስቀድሞ በክስ መቃወሚያነት ቀርቦ ብይን የተሰጡበት በመሆኑ እና ከላይ እንደተገለፀው ከጅምሩ 2ኛ ተከሳሽ የወንጀል ደርጊቱ ተፈፀመ በተባለበት ቦታ እና ጊዜ ያልተገኙ እና የተባለውን የወንጀል ድርጊት ያልፈፀሙ መሆናቸውን በስማቸው መ/ምስክሮች ያስረዳሉ ለመሆኑ ፍ/ቤቱ 2ኛ ተከሳሽ በአማራጭነት ያስያዙትን ጭብጥ እና በዚህ ጭበጥ ላይ የተሰሙትን  መ/ምስክሮች  ቃል መመርመሩ አስፈላጊ ሆኖ ስላለገኘው አልመረመረውም፡፡

1ኛ ተከሳሽን በተመለከተ የቅጣት አስተያየት ዓ/ሕግ ተከሳሽ ጥፋተኛ የተባሉበት ድንጋጌ ደረጃ እና እርከን ያልወጣለት በመሆኑ ወንጀሉን ከፊትም ማስመለጥ ስለሆነ እና ሊገኝ ከታሰበው ጥቅም አንፃር ደረጃው መከላከለኛ ተብሎ እንዲያዝል ወንጀሉ በጋራ የተፈፀመ በመሆኑ በወ/ህ/አ/84(1)መ መሰረት አንድ ማክበጃ እንዲያዝልን ብለዋል፡፡

1ኛ ተከሳሽ ቅጣት ቀሎ እንዲወሰንልኝ በማለት የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቧል
ዓ/ሕግ የቀረበው  ማስረጃ ቢያያዝ ቃቃወሞ የለንም ብሏል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

2ኛ ተከሳሽ ካቀረባባቸው ክስ በነፃ እንዲሰናበቱ ፍርድ የተሰጠ በመሆኑ 2ኛ ተከሳሽ ያስያዙት የዋስትና ገንዘብ ተመላሽ እንዲደረግላቸው ታዟል፡፡

2ኛ ተከሳሽ ከሀገር እንዳይወጡ የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ትዕዛዝ ለሚመለከተው አካል ይፃፍ፡፡

- 1ኛ ተከሳሽ ጥፋተኛ የተባሉ በመሆኑ በፖሊስ ጣቢያ እንዲቆይ ታዟል፡፡

- መዝገቡ ተቀጥሮ የነበረው በትላንትናው ዕለት ቢሆኑም የበዓል ቀን የተቀጠረ በመሆኑ በዛሬው እለት በ25/08/2014 ዓ.ም ተነቧል
- 1ኛ ተከሳሽን በተመለከተ መዝገቡ መርምሮ የቅጣት ውሳኔ ለመስጠት ቀጠሮ ለ28/08/2014 4፡00

የማይነበብ የዳኛ ፊርማ አለበት

ቤ/በ

01/09/14

የ/መ/ቁጥር 286093

ቀን 28/08/2014 ዓ/ም

የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 11ኛ ወንጀል ችሎት

ዳኛ አይናለም ደረጀ

ከሳሽ፡ የፌ/ጠ/ዐቃቤ ህግ

ተከሳሾች 1ኛ. ታረቀኝ ሙሉ ካጨሮ

2ኛ. ደስታ መስፍን መኮንን በነፃ ተሰናብተዋል

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው 1ኛ ተካሳሽን በተመለከተ የቅጣት ውሳኔ ለመስጠት ሲሆን ፍ/ቤቱም በግራቀኙ የቀረበውን የቅጣት አስተያየት ከህጉ ጋር በማገናዘብ ከመረመረ በኃላ የሚከተለው የቅጣት ውሳኔ ሠጥቷል፡፡

<u>ቅ ጣ ት</u>

1ኛ ተከሳሽ በሰው የመነገድ እና ሰውን በህገወጥ መንገድ ድንበር የማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በወጣውን አዋጅ ቁጥር 1178/2012 አንቀፅ 14(1) ስር ምስክሮች በፍ/ቤት የክርክር ሂደት ምስክር ሆነው እንዳይቀርቡ በማይገባ ጥቅም በመደለል ጣልቃ በመግባት በመከልከል ወንጀል ጥፋተኛ የተባሉ ሲሆን ተከሳሽ ጥፋተኛ የተባሉበት ድንጋጌ ደግሞ ከሶስት አመት እስከ ሰባት በሚደርስ ፅኑ እስራት የሚያስቀጣ ነው፡፡ እንደሚታወቀው የቅጣት ውሳኔ ሊሰጥ የሚገባው የወንጀል ህጉን አጠቃላይ መርህ እና አለማ ሊያሳካ በሚያስችል መልኩ ሊሆን የሚገባ ሲሆን ይህን የህጉን አላማ ለማሳከትም ቅጣቱ ሲወሰን በወ/ህ/አ 88/2/ ስር የተመለከቱትን ሁኔታዎች ማለትም የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኝነት መጠን፣ ያለፈ የህይወት ታሪኩን፣ ወንጀል ለማድረግ ያነሳሱትን ምክንያችና የአሳቡን ዓላማ፣ የግል ኑሮውን ሁኔታ፣ የትምህርቱን ደረጃ፣ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነትና የአፈጻጸሙን ሁኔታዎች በማመዛዘን ሊሆን ይገባል፡፡ 1ኛ ተከሳሽ ጥፋተኛ የተባሉበት የህግ ድንጋጌ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ውስጥ ደረጃ ስላልወጣለት በመመሪያው አንቀጽ 20 መሰረት ፍ/ቤቱ ቅጣቱን ሰርቷል፡፡ ዓ/ህግ ወንጀሉ ከፍትህ ማስመለጥ ስለሆነ እና ሊገኝ ከታሰበው ጥቅም አንፃር አንጻር ደረጃው መካከለኛ ተብሎ እንዲያዝል በማለት የጠየቀ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ተከሳሽ የፈፀሙት የወንጀል ድርጊት ምስክሮች በፍ/ቤት ቀርበው እንዳይመሰክሩ በማድረግ ወንጀለኛን ከፍትህ ማስመለጥ ድርጊት ተከሳሽ የተከሰሱበትን እና ጥፋተኛ የተባሉበትን ወንጀል የሚያቋቁመ በመሆኑ እንዲሁም ደረጃው መካከለና ወይም ከፍተኛ የሚባልበትን በቂ ምክንያት ስላላገኘ አጠቃላይ የወንጀል አፈፃፀሙን ሁኔታ በማየት በቀላል የወንጀል ደረጃ መድቧል በመሆኑም ሶስት ዓመት የእስራት ቅጣትን በመነሻነት ይዟል ።ይህም በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 የቅጣት እርከን ሰንጠረዥ ውስጥ እርከን 14 ስር ያርፋል፡፡

ፍ/ቤቱ ቅጣቱን ለመወሰን የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት የጠየቀ ሲሆን ዐ/ሕግ ተከሳሽ የወንጀል ድርጊቱን በጋራ የተፈፀመ በመሆኑ በወ/ህ/አ 84(1)(መ) መሰረት በቅጣት ማክበጃ ምክንያትነት ይያዝልን በማለት አመልክቷል፡፡ ነገር ግን 1ኛተከሳሽ የወንጀል ድርጊቱን

በጋራ በተደረገ ስምምነት የወንጀል ገ,ድርጊቱን ፈፅመዋለወ በሚል የጥፋተኝነት ፍርድ ያልተሰጠ በመሆኑ በዐ/ህግ በኩል የቀረበው የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ተገቢ ሆኖ ስላላገኘው ፍ/ቤቱ የቀረበውን የቅጣት ማክበጃ ምክንያት አልተቀበለውም፡፡
በሌላ በኩል 1ኛ ተከሣሽ ከዚህ በፊት በወንጀል ተከሰው በፍ/ቤት ጥፍተኛ የተባሉበት የወንጀል ሪከርድ ማስረጃ አለመቅረቡ ከዚህ በፊት የነበራቸው ባህሪ መልካም እንደሆነ የሚገመት በመሆኑ ፍ/ቤቱ በወ/ህ/አ/82/1/ሀ/ መሠረት ይህን ምክንያት እንደ አንድ የቅጣት ማቅለያ በመውሰድ እርከኑ ወደ አስራ ሶስት ዝቅ እንዲል ተደርጎል፡፡
1ኛ ተከሳሽ የቤተሰብ አስተዳዳሪ ስለመሆናቸውን ማስረጃ የቀረበ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ይህን ምክንያት በወ/ህ/አ 86 መሰረት በልዩ የቅጣት ማቅለያነት በመያዝ እርከኑ ወደ አስራ ሁለት ዝቅ አድርጎታል፡፡
1ኛ ተከሳሽ በበጎ አድራጎት ስራዎች ሚሳተፉ ስለመሆኑ ማስረጃ በመቅረቡ በወንጀል ህግ አንቀጽ 86 መሰረት እንደ አንድ የቅጣት ማቅለያ ምክንያትነት በመውሰድ እርከኑ ወደ አስራ አንድ ዝቅ አድርጎታል፡፡
1ኛ ተከሳሽ ሌሎች ያቀረባቸው የቅጣት ማቅለያ ምክንቶች እና ማስረጃዎች የማስረጃ ድጋፍ ያላቸው የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ባለመሆናቸው ፍ/ቤቱ አልተቀበላቸውም፤፡
በተያዘው ሶስት የቅጣት ማቅለያ ምክንያት የእስራት ቅጣቱ ካረፈበት እርከን 14 ላይ ሶስት እርከን ሲቀነስ እስራቱ  እርከን 11 ላይ ያርፋል፡፡ ይህም ከአንድ ዓመት ከስምንት ወር እስከ ሁለት ዓመት ከሁለት ወር እስራት ቅጣት ለመወሰን የሚያስችል ሲሆን በዚህ ፍቅድ ስልጣን ውስጥ ፍ/ቤቱ የተከሳሽን ግላዊ ሁኔታ እና የድርጊቱን አፈጻጸም ከግምት በማስገባት 1ኛ ተከሳሽ በአንድ አመት ከስምንት ውር ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ተወስኗል፡፡
ሌላው 1ኛ ተከሳሽ ቅጣቱ እንዲገደብላቸው ያቀረቡትን ጥያቄ በተመለከተ ፍ/ቤቱ ቅጣቱ ሊገደብ የሚችልብትን አሳማኝ ምክንያት ስላላገኘ ጥያቄውን አልተቀበለውም።

**ትዕዛዝ**

- የአዲስ አበባ ማ/ቤት በ1ኛ ተከሳሽ ላይ የተላለፈውን የአንድ ዓመት ከስምንት ወር ፅኑ እስራት ተከሳሽ በዚህ ጉዳይ በፖሊስ ጣቢያ የታሰሩበት ጊዜ የሚታሰብ ሆኖ ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ታዟል፡፡
- 1ኛ ተከሳሽ የስያዙት የዋስትና ገንዘብ ተመላሽ እንዲደረግላቸው ታዟል።
- ይግባኝ መብት ነው ተገልጸል፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል፡፡